ከፈረንሳይኛ የተተረጐመ – የሠልጣኞች መግለጫ መድረክ

ጤና ይስጥልን ክቡራን ተመራጮች ፤

የፈረንሳይኛ ሠልጣኝ የሆነው እኛ ከትውልድ አገራቸው የተሰደዱ ሰዎች ነን። አዲስ ሕይወት የምንጀምርበትን ቦታ በፈረንሳይ አገር ውስጥ አግኝተናል። ከሕብረተሰቡ ጋር እንድንቀላቀል እና በሥራ ዓለም ውስጥ እንድንገባ ፈረንሳይኛን መማር እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው።

ሆኖም ግን እየተወራ ያለው ስለውጭ አገር ዜጎች እና ከሕብረተሰቡ ጋር የመዋሃድ ሁኔታዎች ማሻሻያ የሕግ ዕቅድ ስለ ነባር የፈረንሳይኛ ትምህርት ሁኔታዎች ያለንን አስተያየት እንድንገልጽ አስገድዶናል።

ስለሆነም ስለሚቀጥሉት ነጥቦች ተኩረታችሁን እንድትሰጡን እንፈልጋለን፤

- <u>**ሁሉም ሠልጣኞች የፈረንሳይኛ ትምህርት የማግኘት ዕድል የላቸውም፤**</u>

  የሥልጠናው አሰጣት ሁኔታዎች ከአስፈላጊነቱ ጋር አይገናኝም

  የሥልጠናውን አገልግሎት ለማግኘት እና ወደሚቀጥለው ደረጃ ለመግባት ወረፋ ስላለ ረጅም ጊዜ ይፈጃል።

  ትናንሽ ከተማዎች የሥልጠና አገልግሎት ላይኖራቸው ስለሚችል አንዳንዴ የመኖሪያ ቦታችንን ለመቀየር ወይም ረጅም መንገድ ለመጓዝ ያስገድደናል።

- <u>**የመማር ማስተማር ሁኔታዎቻችን መልካም አይደሉም፤**</u>

  ብዙ ጊዜ በአንድ ክፍል ውስጥ የትምህርት ደረጃ ክፍፍል ትክክል አይደለም። በአንድ ክፍል ውስጥ የሚማሩት የሠልጣኞች የእውቀት ደረጃ የተለያዩ ናቸው።

  ብዙ ጊዜ በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉት የሠልጣኞች ብዛት በርከት ያለ ነው። 15 ሰው ወይም ከዚያ በላይ በሚገኙበት ክፍሎች መማር ከባድ ነው።

- <u>**አንዳንድ ጊዜ ሥልጠናዎቹ የማይመቹን የሆናሉ፤**</u>

  የየግላችን ሁኔታ አንዱ ከአንድኛው ይለያያል።

  አንዳንድ ሠልጣኞች በትውልድ አገራቸው ዩኒቨርሲቲ የተማሩ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ትምህርት ቤት ሄደው የማያውቁም ናቸው። የትምህርታችን ሁኔታ የተለያየ ስለሆነ የሚያስፈልገንም የቋንቋ እውቀት የተለያየ ነው። በሌላ በኩልም ለመማር ያለን ነጻ ጊዜ አንድ አይነት ላይሆን ይችላል። በOFII የተሰጠው የቋንቋ ትምህርት በፍጹም በቂ ስላልሆነ ሁሉም ሰው ለየራሱ ምቹ የሚሆነውን ትምህርት አያገኝም።

  ሥልጠናዎችን በቋንቋ ደረጃ መሠረት ብቻ ማዘጋጀት በቂ አይደለም።

የተለያዩ ሥልጠናዎች መዘጋጀታቸው አስፈላጊ ነው። ጥብቅ የሆኑ በሳምንት የ30 ሰዓት ትምህርት ያካተቱ ሥልጠናዎች፣ በሳምንት የ6 ሰዓት ትምህርት ያካተቱ ሥልጠናዎች፣ በእናት ቋንቋ የተዘጋጁ ሥልጠናዎች፣ በንግግር ችሎታ ላይ፣ ለምሳሌ ያህል በመፃፍ ችሎታ ላይ፣ በትምህርት ዓለም ላይ ወይም በሥራ ዓለም ላይ ተኩረት የሚሰጡ ስፔሻላይዝድ የሆኑ ሥልጠናዎች ወይም ደግሞ የንግግር ወርክሾፖች አስፈላጊ ናቸው።

- **<u>የጨቅላ ህፃናት ሞግዚት የማግኘት መንገዶች ጠባብ ናቸው</u>**

  ህፃን ልጆች ያላቸው ሠልጣኞች ብዙ ጊዜ በህፃናት ማዋያ ቦታ ውስጥ ቦታ እስኪመደብላቸው ድረስ ትምህርታቸውን የማቋረጥ ሁኔታ ያጋጥማቸዋል።

- **<u>ከዚህ ቀደም የነበሩን የትምህርት ማስረጃዎቻችን ተቀባይነት አያገኙም</u>**

  በተማርንበት ሙያ መቼም ልንሠራ እንደማንችል እያወቅን ፈረንሳይኛን የመማር ጉጉት እንዴት ሊኖርን ይችላል?

- **<u>የአሠልጣኞች የሥራ ሁኔታ ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ነው</u>**

  የአሠልጣኞች የሥራ ሁኔታ በሠልጣኞች ላይ ተፅዕኖ ይኖሯል።

  ለኛ በጥሩ ሁኔታ ክትትል እንዲያደርጉልን የተመደቡላቸው ቁሳቁሶች በዓላማዎቹ እና በተለያሉ ሠልጣኞች አስፈላጊነት መሠረት በቂ መሆን አለባቸው። የአሠልጣኞች የአስተዳደራዊ የሥራ ጫና ብዙ ነው።

  ትምህርቱን ለማዘጋጀት እና የሠልጣኞች ክትትል ለማድረግ በቂ ጊዜ የማያገኙባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው።

  በእንደዚህ አይነት የሥራ ሁኔታ ለመሥራት ከሆነ አሠልጣኝ የመሆን ፍላጎት ማን ሊኖረው ይችላል?

- **<u>በጎ ፍቃደኞች አብዛኛውን ጊዜ ብቻቸውን ስለሚሠሩ ችግር ይሆንባቸዋል</u>**
  የመቀበያ እና የሥልጠናው አብዛኛው ክፍል ለነዚህ ሥራዎች ያልሠለጠኑ ሊሆኑ በሚችሉ በጎ ፍቃደኞች ኃላፊነት ሥር ነው። ለበጎ ፍቃደኞቹ ሁልጊዜ ሥልጣና ሊሰጣቸው ይገባል።

  ሥራቸው እና የመርዳት ፍላጎታቸው በጣም ደስ ቢለንም በባለሙያ ለሚሰጥ ትምህርት የማሟያ ሥራ መሆን አለበት ።

  በጎ ፍቃደኞች ከፈረንሳይኛ ትምህርት ማስተማር በስተቀር ሌላ ኃላፊነት ሊሰጣቸው ይችላል። ለምሳሌ ያህል ሌላ አስፈላጊነት ወይም ፍላጎት ለማሟላት የሚፈቅዱ የመዝናኛ ወይም የባህል እንቅስቃሴ የማዘጋጀት ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ። በተጨማሪም እነዚህ እንቅስቃሴዎች እንደሌላ የመማሪያ መንገዶችም ሊቆጠሩ ይችላሉ።

ፈረንሳይኛን ለመማር፣ እዚህ ሕይወታችንን መልሶ ለመገንባት እና ለሕብረተሰቡ ተሳትፎአችንን ለመጨመር እጅግ ፍላጎት አለን። ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ በፈረንሳይኛ ትምህርታችን ሂደት ላይ ብዙ እንቅፋቶች ስለሚያጋጥሙን አንዳንዶቻችን ተስፋ እንቆርጣለን።

**የፈረንሳይኛ ትምህርት ሠልጣኞች በመሆናችን ረገድ የሚቀጥሉትን ነገሮች እንዲሟሉልን እንጠይቃለን**

- **በፈረንሳይ አገር አቀፍ የተዘጋጁ ባለሙያ በሆኑ አሠልጣኞች የተሰጡ የፈረንሳይኛ ትምህርቶች፣**
- **የተለያዩ ለኛ አስፈላጊ ለሚሆኑ የተለያዩ ሥልጠናዎች፣**

- **ለሠራተኞች እና ለፎርማስዮ ፕሮፌስዮኔል የተባለ መደበኛ የሙያ ትምህርት ሠልጣኞች የሚሰጣቸው የቀድሚያ መብት ተመሳሳይ የሆነው የህፃናት ማዋያ ቦታ የመመደብ መብት፤**

- **ከዚህ ቀደም የነበሩን የትምህርት ማስረጃዎች ተቀባይነት እንዲያገኙ፤**

ይህ መድረክ በፈረንሳይ አገር ውስጥ ፈረንሳይኛ እየተማሩ ባሉ ሰዎች ታስቦ የተፃፈ ነው። ለፍራንሴ ፑር ቱስ ማለትም ፈረንሳይኛ ለሁሉም የተባለ ማኅበር የሚያከናውን ጥናት እና እንቅስቃሴ ተሳታፊዎች ናቸው። *ሥራውን* የጀመረችው ጉልተን ቦያጂ (Gülten Boyaci፥ ሊጎስሃይም በሚገኘው የአልባትሮስ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ማዕከል አባል) ስትሆን ቀጥሎም ሳላህ ኢሳ (Salah Issa፥ ኞር ከተማ በሚገኘው የኮራፕሊስ ማኅበር አባል) እና ረድዋን ኢድሪስ (Radwan Idriss፥ የቴር ከተማ የፍረንሳይ እና የሱዳን የባህላዊ እና የመረዳዳት ልውውጥ ማኅበር አባል) ተሳታፊዎች ሆነዋል። ሦስቱ ሰዎች ከሚያውቋቸው ሠልጣኞች ጋር ባደረጉት ውይይት መሠረት ይህንን ፅሑፍ ፀፈዋል።